# የአይጥና የድመት ጋብቻ

25-28ኛው ሳምንት

1ኛ ክፍል

መጽሐፍ 12



# የአይጥና የድመት ጋብቻ

መጽሐፍ 12 | 1ኛ ክፍል | 25-28ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ::

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



አይጦችና ድመቶች አዳኝና ታዳኝ ናቸው፡፡



አይጦች አዳኝነትና ታዳኝነት እንዲቀር ፈለጉ:: ስለዚህ እርቃቸውን በጋብቻ ለማጠናከር ተስማሙ:: በሴትና በወንድ ወገን ዝግጅት ተጀመረ::



የሰርጉ ቀን ደረሰ፡፡
ሁለቱ ሙሽሮችና ሚዜዎች
ተውበዋል።



ድመቶች አይጦችን አዘናግተው
ለመፍጀት መከሩ፡፡ ቀልጣፋ
ሚዜዎች በብዛት ተመረጡ፡፡

አንዲት ብልጥ አይጥ አይጦችን አስጠነቀቀች። "ያልጠረጠረ ተመነጠረ እንዳይሆን" አለች።

ሁሉም በየፊታቸው ጉድጉዋድ ቆፈሩ። የድመት ሚዜዎች እየሮጡ ወደ አይጦች ዳስ ተጠጉ። አይጦችን ለመያዝ በጣም ተጣደፉ።

“ጎረምሳ፣ የድመት ጎረምሳ፣
አሃ! እስቲ አንዳንዱን አንሳ”
አሉ።

አይጦችም በተራቸው “እኛም
አውቀናል፤ ጉድጉዋድ ምሰናል”
አሉ።



በመጨረሻም ድመቶች “እንቅ! እንቅ!” አሉ::

አይጦችም “ጥልቅ! ጥልቅ!” በማለት ሁሉም ወደጉድጓዋድ ውስጥ ገቡ:: ድመቶችም አይናቸውን አፍጥጠው ቀሩ::

USAID
ከአሜሪካን ህዝብ